*AMHARIC*

SEATTLE PUBLIC SCHOOLS

## ለ 2009-2010 የትምህርት አመት የጸደቀ አዲስ የአውቶቡስ መነሽና መድረሻ ሰአቶች

በ ሰኔ 3 በትምህርት ቤቶች ቦርድ ስብሰባ ላይ፡ የቦርዱ አባላት ለ 2009-2010 የትምህርት አመት አዲስ የመነሻና የመድረሻ ሰዓቶች እንዲኖሩ በሰጡት ድምጽ አጽድቀዋል። ይህ ደግሞ ሁሉም ትምህርት ቤቶች ትምህርት የሚጀምሩበትንና የሚጨርሱበትን ሰዓቶች የሚቀይር ነው።

ይህ ውሳኔ በመጋቢት 18 ለሲያትል ትምህርት ቤቶች አዲስ የትራንስፖርት መመዘኛን በሚመለከት፡ በትምህርት ቤቶች ቦርድ የጸደቀውን በተግባር ለማዋል ነው። የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች አውቶቡስ የሚጫኑበትንና የሚወርዱበት ሰአት ፡ ሳይጨልም ብርሃን እያለ አንዳንድ ተግባሮችን ለማድረግ የሚችሉበት እንዲሆን ከቤተሰቦች የቀረበውን አስተያየት ሰምተናል። ከዚህ ከተገኘው አስተያየት በመነሳት ሁሉም ትምህርት ቤቶች ትምህርት የሚጀምሩበት ሰአት ከ 10-15 ደቂቃ ያህል ቀደም ብሎ እንዲሆን የጊዜ ሰሌዳ መሻሻል እንዲደረግበት ሓሳብ እናቀርባለን።

የትራንስፖርት አገልግሎትን በሚመለከተ የተደረገ ይህ መምዘኛ፡ የአያሌ ተማሪዎች በአውቶቡስ የሚጓጓዙበትን ሰአት እንዲቀንስ ያደርገዋል፤ የጊዜ ሰሌዳን በሚመለከት በይበልጥ ቀጣይነት ያለውና አስተማማኝ እንዲሆን ያደርጋል፡ እንዲሁም በአቶቡስ መስመሮች የሚያሽከረክሩ ሾፌሮች ቀጣይነት እንዲኖራቸው ያደርጋል። ይህ ለውጥ እንዲሁ በሲያትል ትምህርት ቤቶች ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸውን ተማሪዎች በ 49 ያነሱ አውቶቡሶች አገልግሎት ለመስጠት ያስችላል፣ የአስተዳደሩን የካርቦን አጠቃቀም እንዲቀንስ ያደርገዋል። እንዲሁም የአሰራርን ቅልጥፍና እንዲጨምርና የትራንስፖርት ወጪ በ $ 2.2 ሚሊዮን እንዲቀንስ ያደርገዋል።

ትምህርት ቤት የሚጀመርበትንና የሚጨረስበትን ሰአቶች በሚመለከት ለውጥ ማድረግ ለሁሉም ቤተሰቦቻችንና ሰራተኞቻችን የጊዜ ሰሌዳን ማመቻቸት እንደሚያስፈልጋቸርው እንረዳለን። በዚህ ምክንያት ነው በመስከረም ወር 2009 ትምህርት ከመጀመሩ በፊት በቂ የሆነ መረጃ አስቀድመን ለመስጠት የፈለግነው።

ከዚህ በታች ትምህርት ቤታችን የሚጀመርበትንና የሚያልቅበትን ሰአቶች እንዲሁም አውቶቡስ ጠዋትና ከቀትር በኋላ የሚደርሱበትንና የሚነሱበትን መረጃ የያዘ ነው። በነሃሴ ወር አጋማሽ አካባቢ ከሲያትል ትምህርቲ ቤቶች የትራንስፖርት ክፍል፡ አውቶቡሶች የሚጭኑበትንና የሚያራግፉበትን ሰአት የያዘ እርግጠኛ መረጃ ለቤተሰቦች ይላክላቸዋል።

http://www.seattleschools.org/area/transportation/times/proposedtranstimes.pdf